# የወያኔ ካድሬዎች ደባና አሸባሪነት በስደት ምድር

አገርና ሰላም ወዳድ የኢትዮጵያ ሕዝብን ትዕግስተኝነት ወያኔ እንደ ፍርሐትና ያለአዋቂነት በመቁጠር በአገር ውስጥ ለ18 ዓመታት ሕዝባችንን በማሰርና በመግደል፣ በማስፈራራትና ሐብት ንብረቱን በመዝረፍ፣ ሰብአዊና ሕጋዊ መብቱን በመገፈፍ ለባሰ ችግር ዳርጎታል። ሞትና እሥራትን በመሸሽ ላይ ያለው ኢትዮጵያዊ ስደተኛን ኬንያና ሱዳን በመሳሰሉት ጎረቤት አገሮች ወያኔ ተከታትሎ ገብቶ በመግደልና በማስገደል፣ እያሳፈነም ወደ አገር ቤት ማስመለሱ፣ ለስቃይና ለእሥራት መዳረጉ ሲገርመን፤ ከነዚህ ከወያኔ አስከፊ ድርጊቶች አምልጠው በዓለም ዙሪያ የተበተነው ኢትዮጵያዊ በተሰደደበት አገር እንኳን የተረጋጋ ኑሮ እንዳይኖር በድንበር ዘለል ካድሬዎቹ አማካይነት በፖለቲካ፣ በዘር፣ በሐይማኖትና በጥቅማ ጥቅም እያደራጀና እየመለመለ ይገኛል። በተለይ በሐይማኖትና በኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ ካድሬዎቹን በአመራር ደርጃ ሰርጎ በማስገባት ለወያኔ ሥርዓት ተገዥነትን ማመቻቸት ካልሆነም ኮሙኒቲዎችና የሐይማኖት ተቋማትን በማፍረስ የነዋሪዎችን የአንድነት ህልውናን ማሳጣት ከጀመረ ውሎ አድሯል። እነዚህ የወያኔ ካድሬዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ስም በልመና የተገኘውን ገንዘብ በመጠቀም የኢትዮጵያውያን የንግድ ድርጅቶችን የወያኔ ደጋፊ እንደሆኑ በማስመሰልና ንግዳቸውን በማዳከም ኅብረተሰቡንም በመከፋፈል፣ የኢትዮጵያውያንን አንድነት በመሸርሸርና ሰላምና ፍቅርን ለመንሳት የተለያዩ ቡድኖችን በማቋቋም በኪነ ጥበብ፣ በመረዳጃ እድር፣ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማኅበር ስም ወዘተ... የዲያስፖራን ላብ ውጤት የሆነውን ገንዘብና ስሜቱን ለመስለብ በተለያዩ ከተሞችና በሳይበርም እንኳን ሳይቀር አያሌ ካድሬዎቹን አሰማርቶ የከፋፋይነት ሥራውን ቀጥሏል። የዚሁ የወያኔ እንቅስቃሴ ደባና ሰለባ ከሆኑት እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ ለሌላው የመንቂያ ደወል ይሆናል ብለን እናምናለን። በካሊፎርኒያ ስቴት በሳንዲያጎ ከተማ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ላይ የወያኔ ካድሬዎችና ሆድ አደር ግለሰቦች የፈጸሙትና እየፈጸሙ ያሉ ከብዙ በጥቂቱ ብንጠቅስ እንኳ፤

1ኛ/ ከሳንዲያጎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ጽላት ይዞ በመሸሽና በስደት ያለውን ምዕመናንን በሁለት በመከፈል በደብሩ ላይ ይህ ነው የማይባል በደል አድርሷል። ነገ ግን በሕዝበ ክርስቲያኑ ጥረት ዛሬ የሳንዲያጎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከወትሮውም በበለጠ እራሱን ችሎና ተጠናክሮ ይገኛል።

2ኛ/ በቅርቡ የሳንዲያጎ ሕዝበ ክርስቲያን የቅዱስ ገብርኤልን ቤተክርስቲያን አስፍቶ ለማሰራት የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት የሕዝቡን አንድነትና ፍላጎት ለመነጣጠል ብሎም ለማደናቀፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። አሁንም በህዝቡ ጥረት ድርጊታቸው ከሽፏል።

3ኛ/ ለረጅም ጊዜ በርካታ አገልግሎቶችን ለኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ያበረከት የነበረውን ኮሙኒቲን በሁለት ከመከፈል ባሻገር ካድሬዎቹ በሰርጎ ገብነት አመራር ከያዙ በኋላ ሁለቱንም ኮሙኒቲዎች አፍርሶ በምትኩ የትግራይ ልማት ማኅበር አቋቁሟል። የትግራይ ልማት እንደስሙ ሳይሆን በተግባሩ የወያኔ ፖለቲካ የጀርባ አጥንት በመሆኑ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሐብት ሆነ፤ ንብረት የግል ባለቤት ከሆነ 18 ዓመት እያስቆጠረ ነው።

4ኛ/ በኢትዮጵያ መኖሪያ ቤት ለመሥራት ሆነ፣ ቦታ ለመመራት ትችሉ ዘንድ በማኅበር መደራጀት አለባችሁ በማለት በርካታ ግለሰቦችን በማደራጀት የወያኔ ደጋፊ እንዲሆኑ ካደረጉ በኋላ የግለሰቦችን ገንዘብ አሰባስቦ ለውጭ ምንዛሪ ይረዳ ዘንድ ለወያኔ ባለሥልጣን አስረክቧል።

5ኛ/ በሳንዲያጎ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ግለሰቦች በረጅም ጊዜ ሂደት ጥረውና ግረው ያፈሩትን የታክሲ ሜዳሊያዎችን (የባለንብረትነት ፈቃድ) ለማስወረስና የግል ባለቤትነት መብት በመጋፋት ስለጉዳዩ ምንም ያልተረዱ በታክሲ ሺፌርነት የሚተዳደሩ ቅን ኢትዮጵያውያን ፊርማቸውን በማሰባሰብና በማኅበር በማደራጀት ወገን በወገን ላይ እንዲነሳ ቅራኔና ጥላቻ እንዲፈጠር ከፍተኛ በደል ለማድረስ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

6ኛ/ በአሁኑ ጊዜ ሁሉንም እያሳዘነ የሚገኘው በወያኔ ቀጭን ትዕዛዝ የመረዳጃ-እድር ሕብረት የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በወያኔ ዋና አቀንቃኞች በከተማ ውስጥ የሚገኙትን የንግድ ተቋማት በመንተራስ ለሚቋቋመው መረዳጃ-እድር ሕብረት ስኬታማነት ደጋፊና እስፖንሰራችን እንድትሆኑ እያሉ ለወያኔ የውጭ ምንዛሬ ለመሰብሰብና የኢትዮጵያውያን መከፋፈያ መድረክ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ ከዚህ በላይ በአንዲት ከተማ የወያኔ ካድሬዎች እየፈጸሙ ያሉትን ለአብነት ስንጠቅስ በየትም ቦታ ያሉ ኢትዮጵያውያን ከቀድሞ በነቃ ሁኔታ ቢቻል በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ተደራጅተን ይህንን የወያኔ ካድሬዎች ደባና አሸባሪነት መከላከል ግዴታችን መሆኑን አውቀን በዝግጁነት መነሳት የሁላችንም ሐላፊነት ነው።

ከደመላሽ ካሳ

ካሊፎርኒያ